# የግንቦት 7 ቀን ምርጫ

ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር)

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፈው ግንቦት 7 ቀን (1997 ዓ. ም.) የሚፈልገውን መርጧል። የታመኑ ማስረጃዎች የሚያመለክቱት የቅንጅት ተወዳዳሪዎች ከ50 በመቶ በላይ ድምፅ በማግኘት አሸንፈዋል። ሥልጣኑን የያዘው ኢሕአዴግ ግን በዚያው በሥልጣኑ ለመቆየት "የተቃዋሚው ቡድን ያሸነፈው በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች እንጂ 80 በመቶው የሚሆነው የሀገር ቤቱ ሕዝብ የመረጠው እኛን ነው" ብሎ አውጇል።

የኢሕአዴግ ዘዴ ለጊዜው ሠርቶለት ነበር፤ "ባላገሩ በእጄ ነው" የሚለውን ፕሮፓጋንዳ ደጋግሞ ያሰማ የነበረው ገና ምርጫው ከመጀመሩ ከብዙ ወራት በፊት ጀምሮ ስለሆነ፥ ምርጫው በተደረገ ማግስት (ማለት ገና የድምፅ ቆጠራው ሳይጀመር) "አሸነፍኩ" ብሎ ሲዋሽ፥ የውጪው ዓለም (ከኢትዮጵያውያንም አንዳንዶች) አምነውት ነበር።

ባላገሩ ከኔ ጋራ ነው የሚሉትን ፕሮፓጋንዳ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ለምን እንዳመኑ አላውቅም፤ የውጪው ዓለም ሰዎች ያመኑት ግን ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ላይ መሸነፉን ሳይገረም መቀበሉን ሲያዩ፥ "በቅድሚያ የተናገረው ግምት እውነትም ልክ ነው፤ እንደገመተው በአገር ቤት ያሸንፋል" ብለው ስለተደለሉለት ነበር። ማለት፥ "የተቃዋሚው ቡድን የሚያሸንፈው በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች እንጂ ከመቶ 80 የሚሆነው የሀገር ቤቱ ሕዝብ የሚመርጠው እኛን ነው" ሲላቸው፥ "የተቃዋሚው ቡድን የሚያሸንፈው ልናጭበረብር በማንችልበት የውጪ ሀገር ታዛቢዎች በሚገኙበት በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች ብቻ ነው፤ ታዛቢ በሌለበት ከመቶ 80 በሚሆነው የሀገር ቤቱ ሕዝብ ላይ ግን የምናደርገውን እኛ እናውቃለን" ማለቱ አልገባቸውም ነበር። ለቅንጅት ምስጋና ይድረሰውና፥ ታዛቢዎች በሌሉበት የተደረገውን ማጭበርበር ከነማስረጃው ወዲያው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ስላቀረበ፥ አሁን የኢሕአዴግን እውነተኛነት መጠራጠር ጀምረዋል። ቅንጅት ሊመሰገን የሚገባው ማስረጃውን በጊዜው በማቅረቡ ብቻ ሳይሆን "በሕዝቡ ላይ የሚፈጸም በደል መቆም አለበት፤ የታገደበት መብቱም መለቀቅ አለበት" ብሎ በአቋሙ በግትርነት በመጽናቱ ጭምር ነው።

ኢሕአዴግ ባለፉት ዓሥራ አራት ዓመታት በገበሬው ላይ የፈጸመውን ግፍ የውጪው ዓለም ስለማያውቅ ነው እንጂ ቢያወቅ ኖሮ "ገበሬው ከኔ ጋር ነው" ሲል መዋሸቱን የቅንጅት ሰዎች በማስረጃ እስኪያስተባብሉ አይጠብቅም ነበር። የጎጃም ገበሬዎች መንግሥት አለን ብለው አዲስ አበባ ድረስ መጥተው አቤት ቢሉ ከዱላ ሌላ ምን አገኙ? በእርዳታ የመጣ ማዳበሪያ የተነገደው በማን ላይ ነው? እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ኢሕአዴግ ትንሽ እንኳን ድምፅ ያገኛል ተብሎ የሚጠበቀው አንዳንድ መንገድ ከወጣባቸውና ቤቶች ከሚሠሩባቸው ከከተሞቹ ነበር እንጂ ገበሬውማ የነፃው ፕሬስ ጋዜጦች እንኳን በማይደርሱበት ጨለማ ውስጥ ታስሮ እንደሚቦጠቦጥ ያውቀዋል። ታዲያ በዚያ ጨለማ በነበረበት ጊዜ "ከጨለማ ነፃ ከሚያወጣህና ረግጦ ከሚገዛህ ከሁለት አንዱን ምረጥ" ሲባል እንዴት ረግጦ የሚገዛውን ይመርጣል ተብሎ ይገመታል?

**ወልደ ሀጕል**

በዚህ አጋጣሚ አንድ ሲከነክነኝ የኖረ ጥያቄ ላነሣ እፈልጋለሁ፤ ለመሆኑ ወያኔዎች እነ ማን ናቸው? የወያኔዎች ማንነት በብዙ ሊያሳስብ የሚገባው ሌሎቻችንን ብቻ ሳይሆን እነሱን እራሳቸውን ጭምር ነው። የወያኔዎችን ጋዜጠኞችና ሌሎችም ብዙ ሰዎች ዲክታተሮች

ይሏቸዋል፡፡ ወያኔዎች ዲክታተሮች ቢሆኑም ዋናው መታወቂያቸው ዲክታተርነት አይደለም፡፡ ዲክታተር እንደ ሶቪየት ኅብረት መሪዎች የሰው ሐሳብ የማይቀበል፥ እሱን በመሰለው መንገድ ለሀገሩ ጥቅም የሚሠራ ነው፡፡ ዝቅ ብዬ እንደምገልጸው፥ እነዚህ ሰዎች ሥራቸው ሁሉ ተለጣፊዎች ፈጥረው የቅኝ ገዢ ሥራ ነው፡፡ በአንድ ሰው ወይም በአንድ ድርጅት ላይ ሊተባበሩ የማይችሉትን የሀገር ልጅ መሆንንና ቅኝ ገዢ መሆንን የሚያስተባብር ምን ፍጥረት ነው? ስለወያኔዎች ካነበብኩና ከሰማሁ ጀምሮ በዓለም ታሪክ ውስጥ ተመሳሳይ መሪ ተነሥቶ እንደሆን ለማወቅ የታሪክ መጻሕፍትን በመመርመር ብዙ ደከምኩ፡፡ አንድም አላገኘሁም፡፡ መጽሐፈ ቀሌምንጦስና መጽሐፈ ኪዳን የተናገሩት ስለኢትዮጵያ ከሆነ፥ "በኋላ ዘመን  የታችኛው ዓለም ገዢ የሚልከው የስሙ መጀመሪያ "መ" የሆነ "ወልደ ሀጕል" (የጥፋት ልጅ) ይነግሣል" የሚሉት ይኸንን የወያኔዎችን መሪ ሳይሆን አይቀርም ከሚል ጥርጣሬ ደረስኩ፡፡

ሥራው ሁሉ "ወልደ ሀጕል" ይሠራዋል ከሚለው በምንም አይለይም፡፡ ጌታው ሰይጣን ከሊቀ መላእክትነት ሲወድቅ ሌሎችን መላእክትንም ይዞ እንጂ ብቻውን አልወደቀም፡፡ ወልደ ሀጕል በታማኝነት የተላከው ለጥፋት ስለሆነ፥ ተልእኮውን ምንም ቢሆን በፈቃዱ አይለውጥም፡፡ ተሳስተው ወይም መስሏቸው ወልደ ሀጕልን የተከተሉ ኢትዮጵያውያን ግን ሀገራቸውን ሲያፈርስ፥ ማንነታቸውን ሲደመስስ አፍዝ አደንግዝ የተደገመባቸው ይመስል እንደመሰለው ሲጠቀምባቸው መሣሪያ መሆን ሀፍረት ነው፡ ብሔራዊ ግዴታቸውን በማሰብ በዚህ ባመቺ ጊዜ፥ "እምቢ፥ አሁንስ በቃ" ማለት ይኖርባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ አምላክ የሰጣቸው ዕድል ጦር እንዲያነሡ ሳይሆን "የምርጫው ውጤት ይከበር" ብለው በሰላም መንገድ እንዲጨክኑ፥  የጨከነውን እንዲረዱ፥ ያልጨከነውን ወላዋይ እንዲያበረታቱ ነው፡፡ አባቶቻችን ነፃነታቸውን ያስከበሩትና እኛንም ነፃ ያደረጉን በገዳይ መሣሪያ ተጋድለው ሲሆን ለኛ ሰላማዊ ተጋድሎ አይበዛብንም፡፡

**ሕዝቡ ለምን ቅንጅትን መረጠ?**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፈው ግንቦት 7 ቀን ቅንጅትን የመረጠው በሁለት ምክንያት ነው፤ አንደኛ የነፃነቱ ጉዳይ ነው፡፡ ኢሕአዴግ በዘር ኢትዮጵያዊ ሲሆን በአስተዳደር ቅኝ ገዢ በተልእኮ የወልደ ሀጕል ፍጡር ነው፡፡ ቅኝ ገዢዎች በመሣሪያ አሸንፈው የሚገዙትን ሀገር ሀብት ወደ ሮማ፥ ወደ ለንደን፥ ወደ ፓሪስ፥ ወደ ሊዝበን፥ ወደ ማድሪድ፥ ወደ ብራስል ... ያግዙ ነበር፡፡ ቅኝ ገዢዎች በያዙት ሀገር ሥልጣን ያለበትን ቦታ ሁሉ የሚይዙ እነሱና ፍርፋሪ የሚጣልላቸው የሀገሬው ሰዎች ናቸው፡፡ አፄ ሱስንዮስ ካቶሊክ በሆነበት ጊዜና በኢጣልያ ዘመን በገዳማቱ ላይ ሳይቀር የተሾሙበት አበምኔቶች የገዢዎቹ አገልጋዮች እንደነበሩ መርሳት የለብንም፡፡ ቅን ገዢዎች ልጆቻቸው እስከከፍተኛ ደረጃ ሲማሩ ለሚገዙት ሕዝብ ልጆች ተመሳሳይ ዕድል አይሰጡም፡፡ ቅኝ ገዢዎች ለሚገዙት ሕዝብ ነፃነቱን በግድ ካልሆነ በውድ አይለቁለትም፡፡

ይህ የቅኝ ገዢዎች ጠባይ ሁሉም ባሁኑዎቹ ገዢዎቻችን ላይ በግልጽ ይታያል፡፡ ሰላማዊውን ሕዝብ በገዛ ሀገሩ ላይ በሰላም እንዳይንቀሳቀስ "ጥቡዕ ልቡ ለቀቲል" በሆነ ልዩ የጦር ኀይል መውረር የቅኝ ገዢዎች ጠባይ መሆኑን ያነበብንና የደረሰብንም እናስታውሰዋለን፡፡ የቅኝ ገዢዎች ልዩ የጦር ኀይል የሚሰለጥነው ከአገሬው ሕዝብ ተመልምሎ መሆኑንም እናውቃለን፡፡ ብቻ ዘመኑ ስለተለወጠና የጦር ሠራዊቱ ስለነቃ ወገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርግ፥ "ለምን በመንገድ ላይ አብረህ ሄድክ፥ ለምን በሰላም ካንድ ቦታ ተሰበሰብክ" ብሎ ወገኑን ለመግደል ለዘመኑ የቅኝ ገዢ ወልደ ሀጕል ይታዘዛል ብሎ ማንም አይጠረጥረው፤ አያደርገውም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፈው ግንቦት 7 ቀን ቅንጅትን የመረጠበት ሁለተኛው ምክንያት የደቡብ አፍሪካ ነጮች ያመጡትን የዘረኝነት ከፋፍሎ መግዛት አንፈልግም ሲል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ምርጫ በዘር የተዘጋጁትን ፓርቲዎች አንኮታኵቶ ጥሏቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ “እኛ ኢትዮጵያውያን ኦሮሞ፥ ወላይታ፥ ሐዲያ፥ አማራ፥ ጉራጌ … መሆናችንን እንደምናውቅ፥ እናንተም በዘር ለመለያየት አለመፈለጋችንን ዕወቁልን፤ ጥቂቶች ቢታለሉላችሁ የሠራችሁት ሥራ ጥሩ መስሏችሁ አትታለሉ፡ ኦሮሞነት፥ ወላይታነት፥ ሐዲያነት፥ አማራነት፥ ጉራጌነት… የሚያመለክተው ባህላችንን ነው እንጂ አንድነታችንን የሚያደክምብን የፖለቲካ ርእዮተ ዓለማችን አይደለም” ሲሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በምርጫ ኮረጆ ውስጥ አሰምተዋል፡፡

## ቅንጅት ለምን ከኢሕአዴግ ጋራ አብሮ አይሠራም?

የቅንጂት መሪዎች ገና ሲጀምሩ በጎሳ መደራጀትን እምቢ ብለው በኢትዮጵያዊነት የተደራጁት ኢትዮጵያዊነትን የሚፈልገውን የሕዝቡን የልብ ትርታ ሰምተው ተጠሪያቸው ሊሆኑላቸው ቃል በመግባት ነው፡፡ አሁን ኢሕአዴግ የሕዝብን ፍላጎት አልቀበልም ሲል፥ ከውጪ ኀይሎች የሚሰማው ተጽእኖ “ለምን ሥልጣን ተካፍላችሁ አብራችሁ አትሠሩም” የሚል ነው፡፡ አነጋገራቸው ያበሳጫል፡፡ ዲሞክራሲ ማለት ያሸነፈው ፓርቲ መንግሥት ሲያቋቁም ነው የሚሉና የሚሉትን ለራሳቸው የሚያደርጉ ኀይሎች ለኛ ዝቅተኛውን ደረጃ ሲመጥኑልን የሚገባን መበሳጨት ሳይሆን መቆጣት ነው፡፡ ብስጪት ይገድላል፤ ቁጣ ነፃ የማውጣት ኃይል አለው፡፡

የኢሐዴግና የቅንጂት ልዩነት መሠረታዊ ነው፡፡ የግራ ክንፍና የቀኝ ክንፍ ፓርቲዎች የሚቀራረቡትን ያህል እንኳን አይቀራረቡም፡፡ ተገዢ ከገዢ ጋራ አብሮ ለመሥራት የሚችለው እንደተለጣፊዎቹ ውርደትን ሲቀበል ብቻ ነው፡፡ የሚተባበሩ ገዳዳና ወልጋዳ ወይም ርቱዕና ሥሙር ናቸው እንጂ ርቱዕና ወልጋዳ፥ ሀገር-ወዳድና ሀገር-ጠላ፥ ወልደ ሀጉልና ወልደ እጓለ እመሕያው አይተባበሩም፡፡ “ኢትዮጵያ አለች” የሚል “ኢትዮጵያ የለችም፥ ካለችም መኖር የለባትም” ከሚል ጋራ እንዴት አድርጎ፥ ለማንስ ብሎ አብሮ ይሠራል? አንዱ ሲገነባ አንዱ ያፈርስና ውሐ ቅዳ ውሐ መልስ ይሆናል፡፡ ያውም ቢሆን ሥልጣኑን እኩል ቢካፈሉ ነው፡፡ ነፃነት ለሕዝብ ለማስገኘት የተመረጠ ፓርቲ ነፃነት ገፋፊውን የማሸነፍ ዓላማውን ለውጦ ነፃነቱን ለገፈፈው ፓርቲ ጥገኛ ሆኖ በግብር አበርነት አይሠራም፡፡ ሕዝቡ ፓርቲውን አደራ ያለው ፥ ፓርቲውም የተዘጋጀው ሕዝቡ ነፃ ለመውጣት በሚያደርገው ትግል እንዲመራው ነው፡፡ አደራን ማክበር ታላቁ ባህላችን እንደሆነ የቅንጅት መሪዎች ያውቃሉ፡፡

“ከፓርላማው ውስጥ ገብቶ ከውስጥ ሆኖ መታገል ይሻላል” የሚል ሐሳብም ሽው ሲል ይሰማል፡፡ “ከተመረጡት የቅንጅት ተወካዮች ግማሾቹን ይዛችሁ፥ ግማሾቹን የትም ለቀን ጅብ ጥላችሁ ግቡ፤ ስለምንፈራላችሁ ተከፋፈሉ” ማለታቸው ነው፡፡ እነማንን ይዘው እነማንን ጥለው ይግቡ? ከገቡ ይከፋፈላሉ፤ ካልገቡ ሳይከፋፈሉ በአንድነት ይታገላሉ፡፡ እነዚህ “እንፈራላችኋለን፥ ተከፋፈሉ” የሚሉ ወገኖች በመከፋፈል የሚያደርጉት ትግል በአንድነት ከሚያደርጉት ትግል የሚያንስ ሆኖ ሳለ በምን እንደሚሻል በቂ ምክንያት አይሰጡም፡፡ ሥጋታቸው ለሚያውቋቸው ለጥቂቶች ሕይወት ነው፡፡ እርግጥ ሕይወትን መንከባከብ የሚገባ ነው፡፡ ግን ከውጪ የሚቀሩትም እኮ የሚንከባከቡለት ሕይወት አላቸው፡፡ በነሱ ላይ ለሚደርሰው የወያኔ በቀል ያሰቡበት አይመስሉም፡፡ ለማናቸውም ትግሉ የሕዝብ ስለሆነ፥ የትግሉን አቅጣጫ የሚወስን ሕዝብ ብቻ ነው፡፡ ግማሻችሁ ገብታችሁ ግማሻችሁ ከውጪ ቀርታችሁ አታግሉን ካለ ከፓርላማው የሚገቡትንና የማይገቡትን እየመረጠ የሚከፋፍል ሕዝቡ እንጂ ወያኔ አይደለም፡፡

## ቅንጅት አዲስ አበባን ለምን አያስተዳድርም?

ከሁሉም የሚያስገርመው ከኢሕአዴግና ከደጋፊዎቹ በተንኮል፥ ከሌላው ዘንድ ደግሞ በፍርሀትና በሞኝነት የሚሰነዘር ሐሳብ፥ “ቅንጅት አዲስ አበባን አሸንፏል፡፡ ይኸንን የአስመራጭ ኮሚቴ ሳይቀር ሁሉም አምኗል፡፡ ታዲያ ለምንድን ነው ቅንጅት የአዲስ አበባን

ቁልፍ ተቀብሎ ከተማይቱን የማያስተዳድረው?” የሚል ነው:: የአዲስ አበባ ከተማ ተጠያቂነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ ነው:: ፓሊሱ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ስር ነው:: አዲስ አበባን ያሸነፈው ፓርቲ ለከተማው የሚያገለግል የመገናኛ ብዙኃን፥ በተለየም ሬዲዮና ቴሌቪዥን ማቋቋም እንኳን አይፈቀድለትም:: እንዲህ ከሆነ፥ ከተማይቱን ማስተዳደር ማለት የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ተላላኪና መንድ ጠራጊ ከመሆን አያልፍም:: ያለው **መፍትሔው አንድ ብቻ ነው፤ ሕዝቡ የምትፈልገውን ምረጥ ተብሎ፥ መርጧል:: የመንግሥት ኃላፊነት ምርጫውን ማክበር፥ የሕዝብ ግዴታ ምርጫውን ማስከበር ብቻ ነው::** ምርጫ የተካሄደው ሕዝብ የፈለገውን መንግሥት እንዲያቋቁም እንጂ፥ የሕዝቡን ፍላጎት ለማወቅ ያህል የተደረገ ቅንቀና (survey) አይደለም::

**ግዴታው የኛ ነው**

ባሁኑ ሰዓት የውጪው ዓለም በኢትዮጵያ ላይ ለምን እንደዚህ እንደጨከነ ብዙዎቻችንን ገርሞናል:: ግን በጉልበታቸው በሕዝብ ማጂራት ላይ የሚሰፍሩትን የሚያስወግድ ሕዝብ ነው እንጂ የውጪ ኀይል አይደለም:: የውጪ ኀይሎችን የምንጠይቃቸው ዲሞክራት ነን ካሉ እንዲህ ያሉ ገገሮችን እንዳይደግፉብን ነው እንጂ እንዲያስወግዱልን አይደለም:: እሱ የኛ ፈንታ ነው:: ከኛ ማህል በውጪ ኀይሎች ተስፋ የጣለ ካለ፥ የተሳሳተ ሐሳቡንና ከንቱ ምኞቱን ካሁኑ መለወጥና ብሔራዊ ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል::

ቅንጅት አዲስ አበባን ባሸነፈ ማግስት፥ ኢሕአዴግ ላንድ ወር ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይደረግ ከለከለ:: የምርጫው ውጤት በይፋ የሚነገረው ሰኔ 1 ቀን ነው ብሎ ካወጀ በኋላ ከምርጫው ማግስት ጀምሮ ማሸነፉን በየቀኑ በመገናኛ ብዙኃን ለሕዝብ ያሰማል፤ ምርጫው ካለቀ ጀምሮ ተቃዋሚ ቡድኖች ከመገናኛ ብዙኃን እንዳይደርሱ ከለከለ:: የተቃዋሚው ቡድኖች ባቀረቡት ማመልከቻ መሠረት ምርጫው እንደገና ይካሄዳል በማለት ጠያቂዎቹን ካስታገሠ በኋላ የኢሕአዴግን አሸናፊነት ማወጁን ቀጠለ:: አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ የምርጫው ውጤት ካንድ ወር በፊት አይነገርም አለ:: ካንድ ወር በኋላ የሚያውጀው ውጤት እስካሁን ለወያኔ ከሰጠው የተለየ የትኛው ውጤት እንደሆነ ማንም በእርግጠኝነት አያውቅም:: ግን እነዚህ ወያኔ የወሰዳቸው እርምጃዎች ሁሉም ሕዝብን ለማሸነፍ በሶሻል ሳይኮሎጂ የተፈተኑ የፖለቲካ ዘዴዎች ናቸው:: እንደሚመስለኝ ዘዴውን ለወያኔዎች የነገሯቸው የምዕራባውያን አማካሪዎቻቸው ሳይሆኑ አይቀሩም::

**ጊዜው አሁን ነው**

በትንሽ ምሳሌ ላስረዳ:: ጀርመን ሀገር ተማሪ በነበርኩበት ዘመን የመካከለኛው አውሮፓ ተማሪዎች ማኅበር ነበረን:: የማኅበሩ ፕሬዚዳንት በነበርኩበት ጊዜ ከስብሰባዎቻችን የአንዱ ሊቀ መንበር ሆኜ ስመራ፥ አንድ ማኅበርተኛ ተማሪ ልብ የሚነካ ንግግር አደረገ:: በዚያን ጊዜ ተቀምጠው ከሚያዳምጡት ተማሪዎች አንዱ ጥያቄ ሊጠይቅ ድንገት ብድግ አለ:: ኀላፊነት ስለነበረብኝ ንግግሩ እስኪያልቅ እንዲጠብቅ ነገርኩት፤ ቅር እያለው ተቀመጠ:: ንግግሩ ካልታሰበው በላይ ጊዜ ወስዶ ሲያልቅ፥ “አርአያ፥ በል ጥያቄህን አሁን ጠይቅ” አልኩት:: ተማሪው “ኤዲያ፥ አሁንማ የተቀሰቀሰው ወኔዬ ከበረደ በኋላ ምኑን ነው የምጠይቀው!” ብሎ ሳይጠይቅ ቀረ:: ይደር የሚባል ሐሳብ ነው እንጂ ትግል የሚካሄደው የፈላው ደም ሳይቀዘቅዝ ነው:: እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች እንደሚሉት ብረትን ለመግራት የሚቻለው ሳይበርድ ነው::

እያንዳንዱ የወያኔ እርምጃ የተቆጣውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ በማብረድና **ተራራ ያከለውን ድፊያ**(momentum) **በማስተንፈስ** ትግሉን ለማቀዝቀዝ፥ ሕዝቡን ለማዘናጋት የተደረገ ዘዴ ነው:: የመጀመሪያው ዕድል ያመለጠው በ139ኙ የምርጫ ጣቢያዎች ሕዝቡ በሌላ ቦታ እንዳደረገው የድምፅ መስጫ ኮሮጆዎቹን በትብብር የሙጢኝ ብሎ ሳይዝ የቀረ ጊዜ ነው:: ጥቂቶች ብዙዎችን ያሳደዷቸውና አሁን የቅንጅት መሪዎችን በአቤቱታ

ኀይላቸውን እንዲያጠፉ ያደረጓቸው በድፍረት ማጣት ከሆነ **ደፋር ያልሆነ ሕዝብ ነፃነት አይኖረውም**:: አሁን ያንን ለማቃናት የሚደረገው ሁሉ ሰዶ ማሳደድ ነው:: ያለፈው አልፏል፤ ለወደፊቱ የቅንጅት መሪዎች የሚሰጡትን ትእዛዝ ለመፈጸም ታጥቆ መጠበቅ ያስፈልጋል:: ወያኔዎች ላንድ ወር የሰላማዊ ሰልፍ ዕቀባ ያደረጉት ተማሪ ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች እስኪዘጉና ተማሪዎች እስኪበተኑ ጊዜ ለማግኘት ነው::

በከተማው ላይ የታጠቀ ወታደር ያዘመቱበት ሕዝቡ ሲሰማና ሲያይ እንደዚያው ድፍረት በማጣት ይገዛልናል ብለው ነው:: ሕዝቡም ያ አንድ ወር እስኪያልፍ የሚጠብቀው ከወር በኋላ ሰላማዊ ሰልፍ የሚፈቀድለት መስሎት እንደሆነ የሚያስተባብል ሌላ ታሪክ አለኝ:: አሜሪካን አገር ሶልት ሌክ ሲቲ ከሚባል ከተማ አንድ ወንጀለኛ ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች በሽጉጥ አስፈራርቶ ካንድ ቦታ ወደ መታጠቢያ ቤት ይወስዳቸዋል:: "ዝም ብላችሁ የምነግራችሁን አድርጉ፤ የምነግራችሁን ካደረጋችሁ ምንም አትሆኑም:: የምነግራችሁን ካላደረጋችሁ ግን ወዮላችሁ አላቸው:: የሚምራቸው መስሏቸው ቃሉን በማመን የሚነግራቸውን ሁሉ አደረጉ:: በሆዳችሁ ተኙ አላቸው፤ በሆዳቸው ተኙ:: ማጅራታችሁን በእጃችሁ ያዙ አላቸው፤ ማጅራታቸውን በእጃቸው ያዙ:: በሆዳቸው ለጥ ሲሉለት እያንዳንዳቸውን በያዘው ሽጉጥ ራስ ራሳቸውን እየመታ ገደላቸው::

መሣሪያ ከያዘ አፈ ጮሌ የሚወጣ ቃልን ሳያምኑ በአመችው ጊዜ መታገል ሌላው ቢቀር ጥቂት ሰው ይድናል:: በጊዜው ካልታገሉት ግን አንድም ሰው አይድንም:: የአዲስ አበባ ሕዝብ እሑድ ለት ሚያዝያ 30 ቀን የወጣውን ያህል ቢወጣ ወያኔ የሕዝቡን መብት በሰላም ከመስጠቱ በፊት ስንቱን ይገድላል? ጊዜ ካገኘ ግን ሁሉንም የሞቱ-ያልሞቱ አድርጎ ሲገዛ ይኖራል:: ሕዝቡ በሕይወት አለ የሚባለው ስለሚተነፍስ ነው እንጂ ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እንደገደለው ነው::

**የድፊያ አስፈላጊነት**

**ድፊያ** ተራራ የማይመክተው ግፊት ነው:: የሕዝብን መብት ለማስከበር የሚያስችለው ድፊያ በየቀኑ እየተነፈሰ ቢሄድም ጨርሶ አልጠፋም:: የሕዝቡ ደም ገና አልቀዘቀዘም:: እሑድ ሚያዝያ 30 ቀን ያበጠው ድፊያ እንዳይተነፍስ የቅንጅት መሪዎች አስፈላጊውን ሁሉ ማድረጋቸው የሚያስመሰግናቸው ነው:: ወያኔ ቀጠሮ እያራዘመ የተገኘውን ድፊያ ለማስተንፈስ ሲሞክር የቅንጅት መሪዎች አጻፋውን በመስጠት ሕዝቡን እስከ ጊዜው እንዳሰፈሰፈና እንደተሰለፈ እንዲቆይ ማድረጋቸው የሚደነቅ ነው:: የሚራዘመውን የወያኔን ቀጠሮ የምንጠብቅ ከሆነ፥ ድፊያውም የሕዝቡ ስሜትም መቀዝቀዙ የማይቀር ነው:: የተገኘው ድፊያ በማምለጡ፥ የተንገዳገደው ወያኔ ተመልሶ እንዲጠናከር ዕድል ከሰጠነው ግን፥ መጽሐፋችን "ወይከውን ደኃሪቱ ለውእቱ ብእሲ ዘየአኪ እምቀዳሚቱ" (የኋለኛው ከፊተኛው ይብስበታል) የሚለው ይደርስብንና ኢትዮጵያን ወደ አለመኖር ስትሄድ በየአለንበት ሆነን እንሰናበታታለን:: መጽሐፋችን ብቻ ሳይሆን ሐኪሞችም ያስጠነቅቁናል፤ "ፔኒሲሊን አትውሰድ፤ ከወሰድክም የታዘዘልህን ሁሉንም ጨርሰህ ውሰድ፤ ሁሉንም ጨርሰህ ካልወሰድክ መድኃኒትነቱ የሚጠቅመው በሽታውን ነው:: መድኃኒቱ በሽታውን ያጠነክረውና ከዚያ በኋላ በሽታውን ለማጥፋት አይቻልም" ይሉናል:: ወያኔዎችም እኮ ካሁኑ በይፋ ተናግረውታል፤ "ከምርጫው ብዙ ነገር ተምረናል" ማለታቸው ይኸንን ፈተና ካለፍን፥ ማለት የተያዘብንን የነብር ጭራችንን እንደምንም አስፈራርተን ካስለቀቅን፥ ሁለተኛ እንዳይደገም እናደርጋለን ማለታቸው ነው:: ሕዝብ ሕይወቱን የሚያገኘው አሁኑኑ በፈተናው ከወደቁበት ሲያስቀራቸው ነው:: ከወልደ ሀጉል ለመላቀቅ ከዚህ የተሻለ ጊዜ ሲመጣ አይታየኝም::

**በምርጫው ያሸነፉ ፓርቲዎችን የሚጠብቃቸው**

ቅንጅትና ኅብረት ይኸንን የጨለማ ዘመን በብዙ ጥበብ እንዲያልፉት ስንጸልይላቸው እኛም ግዴታችንን እየተወጣን መሆን አለበት። "ኢትዮጵያ አንድ ነች" ብሎ የሚነሣ ኀይል ጠላቶቹ ወያኔዎች ብቻ አይደሉም። በኤርትራ፥ በሱማሌ፥ በኦሮሞች ያሉ የጎሳ ፖለቲከኞች፥ የምዕራቡን ዓለም ጨምሮ አያርፉለትም። በዘንድሮው ምርጫ ያሸነፉ ፓርቲዎችን መቃወም የኢትዮጵያን አንድነት መቃወም ነው። እነዚህ ሕዝብ የመረጣቸው ፓርቲዎች "ባንድነት ሆነን ራሳችንን እንቻል" ሲሉ፥ ከነሱ ሌላ ኩሩ ሕዝብ ሊኖር የማይወዱ ሁሉ ጠላት ይሆናሉ። በዚያ ላይ ከጥንት ጀምሮ የሚጠሉትን የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን የሚከተሉትን ኢትዮጵያውያን መብት ያስጠብቁ ይሆናል ተብለው ይፈራሉ። ጎሰኞች ግን እነዚህ ድል አድራጊ ድርጅቶች ባወጡት መድረክ መሠረት የኢትዮጵያ አንድነት ቢመሠረት የሚፈሩት መድረኩን ባለመረዳት ነው። እኔ እንደማውቀው፥ እነዚህ ድል አድራጊ ድርጅቶች ሥልጣን ቢይዙ፥ ጎሳዎች  እንገንጠል ካላሉ በቀር ማንኛቸውንም ጥያቄዎች በሚገባ ይመልሳል። የነሱን ጥያቄ መመለስ ጥቅሙ ለነሱ ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ለድርጅቶቹም ነው።

ቅንጅትና ኅብረት የብሔራዊ መንግሥት ሥልጣን የሚይዙት በሕዝብ ፍላጎት ስለሆነ መንግሥታቸው ከሁሉ አስቀድሞ ያደርጋል ብዬ የምገምተው ቂም በቀል የማይነሣበት የዕርቅ በዓል ነው። ይህ በታሪካችን የተለመደ ነው፤ አንድ ንጉሥ አልፎ ሌላ ንጉሥ ሲተካ መጀመሪያ የሚያውጀው ዐዋጅ "በዱር በገደል ያለህ ግባ፤ ምሬሃለሁ። የሞትነም እኛ፥ የነገሥነም እኛ" የሚል ነው። በዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የዕርቅ ዐዋጅ ቢታወጅ ለሀገሪቱ ሰላምን ከማስገኘቱ ሌላ በሀገር ውስጥም ያለው ሆነ የተሰደደው ሁሉም ተጸጽቶ ለሀገሩ እድገት በትጋት እንዲሠራ ያደርጋል።

ሁለተኛው እርምጃ የአስመራጩን ኮሚቲና የመገናኛ ብዙኃኑን ነፃ ማድረግ ነው። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፓርቲ ቢቋቋም የመገናኛ ብዙኃኑ ለሕዝብ ልቅ ቢሆን የጎሳ ፖለቲካ መሪዎች ሀገሪቷን ሊያፈራርሷት ይችላሉ የሚለው ፍራቻ ነበረ፤ እኔም እውነት ይመስለኝ ነበር። ፍራቻው መሠረት የሌለው መሆኑን የግንቦት 7 ቀን ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ አረጋገጠልኝ። ሕዝቡ የሚፈልገው ዲሞክራሲያዊ አንድነትን ነው። በመሣሪያ ኀይል ካልተገደደ በቀር የኢትዮጵያን መከፋፈል አይቀበልም።

የቀረው በየተራው ይመጣል። የማይመጣው ከዲሞክራሲ ውጪ የሚሠራ ሥራ ብቻ ነው።